# ምዕራፍ ሶስት፡ የአቶ መለስ ትዝታዎች

## 3.1 የመለስ ውበቶች!

የትብዝና ወራታቸውን እና የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ለትግሉ የሰውት አቶ መለስ ዜናዊ በአፀደ ክተለዩን አመታት ተቆጠሩ። አቶ መለስ በህይዎት ዘመናቸው የመሰላቸውን አድርገው ለማንም ወደ ማይቀረው በጊዜ ሄደዋል። ሰውየው የመንግስቱ ሃይለማርያምን ወንበር ተረክበው ከፊተኛቸው ሶስት አመት ዘለግ አድርገው ታላቋን ሃገር ሲያስተዳድሩ እንዳልክ ተብለው፣ የወደዱትን አድርገው፣ በሁሉን አወቅ ልዕለ-ሰብ ተመስለው ነበር። ከማድንቅ እና መታዘዝ አልፈው እንደማምለክ የሚቃጣቸው ተከታዮችንም አትርፈው ነበር። ለዚህም ይመስላል ተከታዮቻቸው መሞታቸውን ላለማመን ከተፈጥሮ ጋር እልህ በሚመስል መልኩ ሬሳ በመኪና ጭነው ጀግና አይሞትም ሲሉ የታዩት።

በኋለኞቹ የመሪነት ዘመናቸው በተለይ የህወሃት/ኢህአዴግ እስትንፋስ፣ የሀገሪቱ ብቸኛ አድራጊ ፈጣሪ፣ ፖሊሲ ቀራጭ፣ ስለሁሉ ተጠያቂ፣ የሁሉ ፈቃጂ ከልካይ፣ ከተሜ ገጠሬውን፣ ልጅ አዋቂውን፣ ሴት ወንዱን፣ ሲጉንም ክንፉንም ሰብሳቢ፣ አወያይ፣ መካሪ ዘካሪ ሆነው ነበር። ፡ ከምርጫ 1997 በኋላ ለትንሹም ለትልቁም በየመድረኩ መታየታቸው ስልጣን ጠቅላይነታቸውን ያሳብቅ ነበር። ሁሉን ጠቅላሎ የመያዙ ነገር አቶመለስን ከሊጡም ከወጡም እንዲሉ በማድረጉ እረፍት ማጣቱ ከህመማቸው ጋር ተደምሮ ሲቀራቸው ወደሞት ሳያጣድፋቸው አልቀረም።

ተማሪውን መለስ ጠቅላይሚኒስተር መለስ ያደረጋቸው ተምሮ ዶክተር ከመሆን የተለምዶ ጉጉት እና ምኞት አለፍ ብለው ማሰባቸው ነው። አቶ መለስ በገብልነት እድሜያቸው እጃቸው የገባውን «ነወር ክበር» የሚያስብለውን የህክምና ዶክተርነት ሙያ እንደምንም ነገር ቆጥረው ደደቢትን መመኘታቸው ሁሉም ሰው የማያስበው ልዩነታቸው ነው።



ደደቢት ከገቡ በኋላም መልካም የሆነውን የማንበብን እጣፋንታ መምረጣቸው ተናግረው እንዲያምርባቸው ረድቷቸዋል። አንባቢነታቸው በነጮች ሳይቀር የሚመሰክርላቸው አቶ መለስ ይበጃል ያሉት ሃሳባቸው ሶስተኛ ወገንን አሳመነም አላሳመነ፣ አስከፋም አስደሰተ፣ ከመርህ ጋር ተጋጨም አልተጋጨ፣ ትናንት ራሳቸው በአንደበታቸው ከተናገሩት ጋር ገጠመም አልገጠመ ዛሬ ያመኑበትን ብቸኛው መንገድ አድርገው ለማስረዳት አይሰንፉም። ይሄ ማንነታቸው ጥሩ ነው መጥፎ ወደ ሚለው ዝርዝር ሳይገባ ላመኑበት ነገር ያላቸው ፅናት ግን ውበታቸው ነበር።

ክፉም ይሁን በጎ ላመነበት ነገር እስከመጨረሻው የሚፀና ሰው እንደሚያደንቁ የሚናገሩት የአቶ መለስ ይህ ንግግራቸው ከላይ የተገለፀውን ማንነታቸውን ያመለክታል። በህልፈታቸው ሰሞን አንድ የቢቢሲ ጋዜጠኛ «ያመኑበትን የሚናገሩ የሚናገሩትን የሚያደርጉ» ሲል ነበር የገለፃቸው። «የሚናገሩትን የሚያደርጉ» የሚለው ቢያጠያይቅም የሚያምኑበትን የሚናገሩ የሚለው ይገልፃቸዋል። ለወትሮው ሲያንቆለጳጵሳቸው የነበረው ዘ-ኢኮኖሚስት መፅሄትም በሞቱ ሰሞን «አምባገነንነትን በአለማቀፍ መድረክ ተቀባይ ለማድረግ ሲለፉ የኖሩ መሪ» ሲል ገልጿቸዋል። ይህ አባባል የመጣው ‹ልማታዊው መንግስቱ በበልጣን ላይ መሰንበትን የሚፈልገው ለልማት ሲል ነው፤ስለዚህ ልማትን እስካመጣ ድረስ ፓርቲየ ስልጣን ላይ ቢቧጅም በልማታዊነቱ ህዝቡ ፈልጎ መርጦት በመሆኑ ዲሞክራሲዊ ከመሆን የሚያግደው የለም› ብለው ሲሞግቱ በመኖራቸው ነው። የፈለገ ተአምር ቢሰራም መንግስት ስልጣን ላይ ከሰነበተ አምባገነንነት እንደማያጣው የሚያውቁት ነጮች ደግሞ ለአምባገነን አገዛዛቸው የልማታዊነት ገበር ያለው የይስሙላ ዲሞክራሲ ካባ የሚሰፉ ከንቱ ደካሚ ሙግተኛ ያደርጓቸዋል።

መንግስታዊ መንበሩን ከመዘወሩ ጎን ለጎን መማርን መሻታቸውም ሌላው የሰውየው መልካም ገፅታ ነው። ትምርቱን ቢማሩም ባይማሩም የሰራዊታቸው ክንድ እስካልዛለ ድረስ በስልጣን ላይ መቆየት እንደሚችሉ እያወቁ መማር መፈለጋቸው ለእውቀት ያላቸውን ቦታ ያመላክታል።

ላይ ይገኛል። በሶስት ዙር በተደረገው ቃለ-ምልልስ ሄንዝ የአቶ መለስን እና የድርጅታቸው ህወሃትን ምስራቃዊ የፖለቲካ ማንነት ሲጠይቃቸው «ድርጅታችን ምስራቃዊነትን አያውቅም፣ ማርክሲስት ሌኒኒስትነትን የሚገልፅ አንዳችም ቅጥያ በድርጅታችን ስም ላይ የለም፤ ምናልባት እኛ በግል ማርክሲዝምን እናምን ይሆናል እንጂ» ሲሉ ነበር እንመሰርተዋለን ሲሉት የኖሩትን ማሌሊትን ዶሮ ሳይጮህ እንደ ጴጥሮስ ደጋግመው የካዱት። ነገሩ ያልጣመው ሄንዝ «ደጋግማችሁ ማርክሲስት ነን ትሉ ነበር፣ እንደውም የአልባኒያን ሶሻሊዝም አርአያ ትግራይ ላይ እንደግማለን ትሉ ነበር» ሲል ሲሞግታቸው አቶ መለስ «እኛ የቻይናንም ሆነ የራሽያን አለያም የአልባኒያን ሶሻሊዝም በህዝባችን ላይ የመጫን እቅድ የለንም» ብለው ከእውነታው የማይገጥመውን ሶሻሊስት አይደለንም ሚለውን አቋማቸውን አጠናክረዋል።

ቃለምልልሱ ከተደረገ ከአንድ አመት በኋላ አዲስ አበባ የገባው ኢህአዴግ ልማታዊ መንግስት ሆንኩ እስካለበት ድህረ ምርጫ 1997 ድረስ ነጭ ካፒታሊዝምን እንደሚከተል አቶ መለስ ደጋግመው ይናገሩ እንደነበር «ዳንዴ» በሚለው መፅሃፍ ላይ ዶ/ር ነጋሶ ገልፀዋል። ካፒታዝምን መከተሉ የምእራባዊያንን ዲሞክራሲ ማስፈንን፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በመንግስት መዳፍ ከመዘወር ለገበያው ሁኔታ መተውን ስለሚጠይቅ እና ይሄ ደግሞ ውስጠ-ማርክሲስት ለሆነው ኢህአዴግ በቀላሉ የማይለመድ መሆኑ ኢህአዴግ አይኑን ሙሉ በሙሉ ከምእራባዊያን ላይ ባያነሳም ቀደምት ምስራቃዊነቱ ከልቡም ስቦት በቅርቡ ወደ ቻይና ጠጋጠጋ ማለት ጀመረ። መሪው አቶ መለስም ቻይናን ከኢትዮጵያ አልፋ ከአፍሪካ ጋር ወዳጅነቷን እንድታጠብቅ በአፍሪካ መድረክ በመወትወት አፍሪካ-ቻይና ወዳጅነትን እውን አደረጉ። የወዳጅነቱ ሁኔታ ቻይናን አንዷን ሀገር አግዘፎ አህጉር ከሆነው ከአፍሪካ ጋር መሳ ያደረገ ያጋደለ ወዳጅነት ነው።

## 3.4 የጫካው እና ከተሜው መለስ

አስራ ሰባት አመታትን በጫካ ትግል ያሳለፈው ህወሃት/ኢህአዴግ አዲስ አበባ ከገባ በኋላም የሚያሳየው የአመራር ዘይቤ ከጫካው አመራር ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ አቶ አስገደ ጨምሮ ከድል በኋላ ኢህአዴግን የተለዩ የቀድሞ ታጋዮች በፅሁፍም ሆነ በሚሰጧቸው ቃለ-ምልልሶች ይገልፃሉ። ይህ መመሳሰል በትጥቅ ትግሉ ወቅት በተለይ በመጨረሻዎቹ ዘመናት



የፖለቲካው ክንፍ ዘዋሪ የነበሩት አቶ መለስ ከድል በኋላም በመሪነቱ በመሰንበታቸው ይሆናል።

የጫካው መለስ ሁልጊዜ አሸናፊነትን ብቻ ሰንቀው የሚነሱ፣ ከእሳቸው ሃሳብ በተቃራኒ የቆመን ሁሉ ተጨባጭ በሆነም ባልሆነም ፍረጃ ከጨዋታ ውጭ እንደሚያደርጉ፣ የተቀናቃኞቻቸውን ግብአተመሬት ለመፋጠን ዋና ዋና መርሆችን እንኳን ከመጣስ እንደማይመለሱ የቀድሞ የትግል አጋራቸው እና የዚህኛው የአቶ መለስ ስብእና ሰለባ የሆኑት አቶ አረጋይ በርሄ አቶ መለስ ባረፉ ሰሞን ለቪኦኤ በሰጡት ሰፊ ቃለምልልስ ገልፀዋል። አቶ ግደይ ዘርአፅዮንንም አቶ መለስ ‹ህወሃት ገላ ላይ የበቀለ ጋንግሪን ስለሆነ እሱ ካልተቆረጠ ህወሃት በህይወት አትኖርም› ብለው እንዳሰናበቷቸው በትግሉ ዙሪያ የተፃፉ መዛግብት ያትታሉ። ይሄ የአቶ ግደይ እና የአቶ አረጋይ እጣ በብዙ ለምን ባይ ታጋዮች ላይም ወድቆ እንደ እስራኤሉ ሙሴ የመሩት ትግል ወደተሰፋ ምድራቸው አዲስ አበባ ሳይደርስ ከመሃል መንገድ እንዲቀሩ አድርጓቸዋል።

የትግሉ ዘመን ገንዘብ ቤት የነበሩት አቶ እየሩስአሌም ጌታቸውም በተመሳሳይ አቶ መለስን ጠላታቸውን ለመወንጀል ራሳቸው ሚያደርጉትን ሳይቀር እንደወንጀል ጠቅሰው የሚከሱ ሲሉ የሃገር ልጅ ለተሰኘው የኢሳት ፕሮግራም ገልፀዋል። በራሳቸው ላይ የደረሰውን እንደማስረጃ ሲገልፁም «ከ1977 በፊት በነበረው የትግሉ ወቅት ከተቃራኒ ጾታ ጋር የፍቅር ግንኙነት መጀመር ክልክል ቢሆንም እኔ በስህተት የጀመርኩትን ግንኙነት ደርሶበት ክሶ አስቀጥቶኝ ነበር። ይህንን ያደረገው ከእኔ ጋር አለመግባባቶች ስለነበሩ እንጂ ህጉን ለማስከበር አልነበረም ምክንያቱም በኋላ አዜብ ራሷ እንደነገረችኝ መለስ እና እሷ ከ1971 ጀምሮ ድብቅ የፍቅር ግንኙነት ነበራቸው» ይላሉ።

ከላይ ስለአቶመለስ የጫካ ስብዕና አፈንግጠው ከወጡት የቀድሞ የትግል አጋሮቻቸው ከሚሰማው በተቃራኒ ስለጫካው መለስ ትህትና፣ ተራማይሌ ሃሳብ አስተናጋጅነት፣ የሁሉን ሃሳብ አድማጭነት፣ ሃሳብን እንጂ ሰውን በክፉ የማያዩ እና ሚዛናዊ ውሳኔ ሰጭ መሪነት የሚመሰክሩ ፀሀፍትም ሆኑ የአይን ምስክሮች ሞልተዋል፡፡ የአቶ መለስን ፖለቲካዊ ስብዕና በተመለከተ በሁለት ተቃራኒ ጫፍ ላይ የቆሙ መረዳቶችን ለማመሳከር የከተሜውን መለስ አመራር ማጤኑ አማራጭ መንገድ ነው።

በግሌ የአቶ መለስን ጉራማይሌ ሃሳብ አስተናጋጅነት ትዕግስት እጠራጠራለሁ። ምናልባት እስከተወሰነ፣ የእሳቸውን ዋናነትእስካተፈታተነ ድረስ የተለየ ሃሳብን የሚቀበሉ ዲሞክራት መሪ ለመምሰል ይሞክሩ ይሆናል እንጂ ለሃሳብ የበላይነት እጃቸውን ሲሰጡ አልተስተዋለም። ይሄን ለማረጋገጥ ደግሞ በራሳቸው አንደበት ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች «ማሰሪያቸው ሲረዝም የተፈቱ ይመስላቸዋል» ሲሉ የገለጹትን እንደአስረጂ ማንሳት ይቻላል።

ጠቅለል ብሎ ሲታይ አቶ መለስን በተመለከተ ዘላቂ ወዳጆቻቸው ከሚያነሱት ፖለቲካዊ ማንነታቸው ይልቅ በነ አቶ አረጋይ የተገለፀው የጫካ ማንነታቸው በከተሜው መለስ ላይ ጎልቶ ይታያል። እንደ ግላዊ መረዳቱ አቶ አረጋይ ‹አቶ መለስ ባለጋራውን ለማጥቃት ማንኛውንም መርህ ሊጥስ ይችላል› ካሉት ነገር እውነትነት በ1997 አቶ መለስ ስልጣናቸውን ለማትረፍ ሲያደርጉት የነበረው ዲሞክራሲያዊ መርሆችን የመጣስ የደመነፍስ ጉዞ ምስክር ነው።

በወቅቱ የተቃውሞው ጎራ መሪዎችን ከያሉበት እየለቀመ (ሲስፈልግም ቦክስ እየሰነዘረ) እስርቤት የሚያጉረው ፖሊስ በቀጥታ የሚታዘዘው በእሳቸው ነበር። የመንግስታቸው አካሄድ የህዝብ ቁጣ ሊቀሰቅስ እንደሚችል የተረዱት ነገር አዋቂው መለስ የዲሞክራሲ መርሆዎች አንዱ የሆነውን የመሰብሰብ መብት በጉዛ አንደበታቸው ላልተወሰነ ጊዜ ብለው ለስምንት አመት እንደ እናት ጡት እንድንረሳው አደረጉ። ጋዜጠኞችን ለቃቅመው ሲያስሩም ከዲሞክራሲያዊ መርሆዎች አንዱ የሆነው ሚዛናዊ መረጃ የማግኘት መብት እየተጣሰነበር።

ከዘጠና ሰባት አለፍ እንበል ከተባለ ደግሞ ለኢህአዴግ ጆሮ የማይመቹ መረጃዎችን የሚያቀርቡ መገናኛ ብዙሃንን ስንት ሃብት አፍስሶ በሞገድ ከማፈን ጀምሮ እስከ ማተሚያ ቤት ድረስ ገስግሶ የውሃሽታ የማድረጉ እርምጃ ዲሞክራሲያዊ መርህ መጣሱ እንደ ቀጠለ ያመላክታል። ህገመንግስታዊ መርሆች ሳይቀሩ ነገሬ የማይባሉበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ሽብርተኝነትን ለመቆጣጠር ወጣ የተባለው አዋጅ፣ የመገናኛብዙሃን እና የሲቪክ ማህበራት ህጎች ለዚህ ምስክሮች ናቸው። ህገ መንግስት ተርጓሚ ተብሎ የተቀመጠው አካልም የአቶ መለስን አመራር የመሞገት ሞገስ ያለው አይመስልም - አይን በአይን ህገመንግስቱን የሚጥሱ ህጎች ሲወጡ በአንዱም ላይ ተቃውሞ ሲሰማ አልተደመጠምና።



አቶ እየሩሳሌም የጫካው መለስ ራሳቸው የሚያደርጉትን ነገር ሳይቀር እንደ ወንጀል ጠቅሰው ተቀናቃኞቻቸውን ይከሱ ይወቅሱበት ነበር ያሉት የአቶ መለስ ስብእና በከተሜው መለስ ውስጥም በጉልህ ይስተዋላል። ራሳቸው አቶ መለስ ይመሩት የነበረው ህወሃት ትግራይን ነፃ ለማውጣት ብረት አንስቶ አስራ ሰባት አመት መዋጋቱ እውነት ቢሆንም እሳቸው መንግስት ከሆኑ በኋላ የወጡበትን ብሄር ነፃ እናወጣለን የሚሉ ድርጅቶችን በጠባብነት ይፈርጁ ነበር። ነፃ አውጭ ነን ባዮቹ ብረት ያነሱ ከሆኑ ደግሞ የስድብ እርግማኑ መጠን ይጨምርና ጠባብ በሚለው ላይ የእንትን ተላላኪ፣ ሃገር አፍራሽ፣ ፀረ-ልማት፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ህዝብ የመሳሰሉ አጠልሺ ቅጥያወች ይጨመሩላቸዋል።

የአቶ መለስ ህወሃት እዚህ የደረሰው ለሻብዕያ አቤት ወዶት ብሎ ቢሆንም አሁን ወደሻዕብያ ጠጋ ጠጋ የሚሉ የኢህአዴግ ባላንጣ ፓርቲዎች ስማቸው ሀገር ከዳተኛ ነው። በጫካ ሳሉ ኢትጵያን ሽራርፎ «ታላቋ ሶማሌ»ን ለመገንባት ደፋቀና ሲል የነበረው ዚያድባሬ በሰጣቸው የሶማሌ ፓስፖርት ሲንቀሳቀሱ እንደነበረ በገዛ አንደበታቸው የተናገሩት አቶ መለስ በተመሳሳይ መንገድ የሚሄዱ የዘመኑ ብረት አንጋች ተቃዋሚዎችን ሲየብጠለጥሉ ጊዜ አይበቃቸውም ነበር።

ተፈጥሯዊው የወጣትነት እድሜ የሚያመጣው ለውጥን መሻት ከዩኒቨርሲቲ ደደቢት ያበረራቸው አቶ መለስ የአሁን ወጣት ስለለውጥ እንዲያስብ አይፈልጉም ነበር። የሚፈልጉት በጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅቶ የእሳቸው መንግስት ባሰበለት መጠን እንዲኖር ነው። እሳቸው እንዳደረጉት ለለውጥ እነሳለሁ ካለ ስሙ አደገኛ ቦዘኔ፣ የሆነ ሰው ተላላኪ (እንጂ በራሱ አስቦ ለውጥ የማይፈልግ)፣ የጎዳና ላይ ነውጠኛ ወዘተ ነው።

## 3.5 ፕሬዚደንት መለሰ

የአስራ ሰባት አመቱን ትግል ደርግን በመጣል ያጠናቀቀው ኢህአዴግ አዲስአበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የሽግግር ወቅት ባለው እና ራሱን ለዘመናት ስልጣን ባመቻቸበት አራት አመት አቶ መለስ የሀገሪቱ ፕሬዚደንት ነበሩ። በዚህ ወቅት ነበር ፓርቲያቸው ስልጣን ላይ የሚሰነብትበትን መደላድል በጥንቃቄ ያበጃጁት። የሽግግሩ ወቅት ሲያበቃ በሰላም እና ዲሞክራሲ ሃይሎች

አሽሙርና ሽንቆጣ አንዳንዴም ፌዝ የተቀላቀለበት መልስ ወደ መስጠቱ ያደሉ ነበር። ለምሳሌ ወደሲሚል የኢትዮጵያን ሰራዊት ስለማዘመት ውይይት ሲደረግ «አቶ ልደቱ በሰአቱ ልጅ ስለነበሩ አያውቁም እንጂ እኛ ለዚያድባሬ አግበን ሃገራችንን አልወጋንም» ሲሉ ልጅ እግር ነኝ በሚሉት አቶ ልደቱ ላይ አፊዘው ነበር። ዶ/ር መረራ ጉዲናም ንግግራቸው እንደዘበት ቢሆንም አቶ መለስን የማስቆጣት አቅም ያለው ጥያቄና ሃሳብ ይሰነዝሩ ነበር። ባልደረባቸው ፕ/ሮ በየነ ጴጥሮስም በሚሰነዝሯቸው ንግግሮች አቶ መለስን በማስቆጣታቸው የሚሸነቁጡ የአቶ መለስን አፀፋ ያስተናግዱ ነበር። በአንድ ወቅት አቶ መለስ ‹እኔ የልጅነት ጊዜየን ለትግል የሰዋሁ እንጂ የግማሽቀን (parc time) ታጋይ አይደለሁም› ሲሉ ፕ/ሮ በየነን እና ሌሎች ተቃዋሚዎችን ለትግላቸው ያላቸውን የቁርጠኝነት ውሱንነት ጠቆም አድርገዋል።

አብዛኛውን ጊዜ አቶ መለስ አክብሮት በተቀላቀለበት እና ለስለስ ባለ ሁኔታ መልስ የሚሰጡት ለአቶ ቡልቻ ጥያቄና አስተያየቶች ነበር። የአባትነት ምክር፣ ስጋት እና ተግሳፅ በሚመስል ድምፀት የሚናገሩት አቶ ቡልቻ ንግግራቸውም ለቁጣ የሚጋብዝ አልነበረም።

## 3.10 ድንጋጤ ያመጣው ኢትጵያዊነትን ማቀንቀን

ህወሃት ገና ከጥንስሱ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ማቀንቀንን ከአማራነት ጋር ብቻ ያገናኝ ነበር። ይህ አባባል የኢትዮጵያን ባለቤትነት ለአማራ ብቻ ማስረከብ ማለት ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ እንደ ሃገር እንድትቆም ደሙን እና ላቡን የገበረው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። አድዋ እና ማይጨው ላይ ለመሞት ሲጠራ ስርግ እንደተጠራ ደስ እያለው ለሃገሩ ነፃነት ሲሞት የተሰባሰበው አማራው ብቻ አልነበረም። የዚህን አባባል እውነትነት ለማረጋገጥ አማራም፣ ኦሮሞም፣ አፋርም፣ ጉራጌም... ያልሆነው የቼኮዝሎቫኪያ ተወላጁ አዶልፍ ፓርለሳክ የፃፈውን እና «የሃበሻ ጀብዱ» በሚል ርዕስ ወደ አማርኛ የተመለሰውን መፅሃፍ ማንበብ ይጠቅማል።

ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሲሆን በፈረስ በበቅሎ ካልሆነ ደግሞ በእግሩ ተጉዞ በቴክኖሎጂም ሆነ በትጥቅ እና ስንቅ አቅሙ ከማይመጣጠነው ጠላት ጋር ተፋልሞ ያቆያትን ሃገር ባለቤነት ለአማራ ብቻ መስጠት ወይ አውቆ እንደ መተኛት ነው አለያም ታሪክን አለማወቅ ነው። ብዙ እንደሚያነቡ



የሚነገርላቸው አቶ መለስ እንግዲህ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን በአማራ ብቻ የሚቀነቀን አድርገው ሲያቀርቡ የነበረበት አካሄድ አውቆ መተኛት እንጂ አለማወቅ ሊሆን አይችልም።

ከ1997 ምርጫ በፊት የህወሃት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ከአማራ ጋር ብቻ የማያያዝ አዝማሚያ በመራው በአቶ መለስ እንደበት እንደ ባንዲራ አይነት ሃገራዊ ምልክቶችን በማጣጣልም ይገለጽ ነበር። በእነዚህ ጊዜያት ታላላቅ ባለስልጣናትን እና የፓርላማ አባላትን ጨምሮ አብዛኛው ህዝብ የሃገሪቱን የህዝብ መዝሙር መዘመር እንኳን ያዳግተው ነበር።

በ1997ቱ ሃገራዊ ምርጫ ቅንጅት በአጭር ጊዜ ገኖ እንዲወጣ ከረዳው ነገር አንዱ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ለመመለስ መንቀሳቀሱ ነበር። ይህን የተረዳው የአቶ መለስ መንግስት የሸፈተውን የህዝብ ልብ ለመመለስ ሲባል ከዕንሰቱ ጀምሮ ከሚታወቅበት ማንነቱ በተቃራኒው ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ማቀንቀን ጀመረ። የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን በየአመቱ ማክበሩ፣ የባንዲራ ቀን እንዲከበር አዋጅ ማውጣቱ ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያው የባንዲራቀን አከባበር በአል አቶመለስ በአካል ተገኝተው ባንዲራ ሲሰቅሉ መታየቱ ሁሉ የበፊቱን ስህተት ለማረም የተደረገ፣ ድንጋጤ ያመጣው የእርምት እርምጃ ነው።

## 3.11 የአቶ መለስ ቁጥብነቶች

ከ1997 በፊት አቶ መለስ በሃገር ውስጥ መድረክ የመታየታቸው ነገር ውሱን ነበር። ይልቅስ ከውጭ ሃገር ከመጡ በስልጣን ተዋረድ የሚያንሷቸውም ቢሆኑ (ከአሜሪካ ከሆነ ደግሞ ሴናተሮችንም ሳይቀር) ለማናገር አይሰንፉም ነበር። ከሶስተኛው ሃገራዊ ምርጫ በኋላ ግን በሃገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ከመበርከታቸው በተጨማሪ ወደ ገጠራማው የሃገሪቱን ክፍል በርካታ ጉዞዎችን አድርገው ነበር። በመገናኛ ብዙሃን ብቅ ብለው የወጣቶችን፣ የሴቶችን፣ የአርቲስቶችን ጉባኤ ሲመሩ፣ ጋዜጠኞችን ሲያነጋግሩ ታዲያ ከሚነሱላቸው ጥያቄዎች ውስጥ ስለባለቤታቸው እና ልጆቻቸው በሚጠየቁት ጥያቄ ላይ ገፍተው ማብራሪያ ከመስጠት ይቆ

ጠቡ ነበር። በልጅነታቸው ካስ መጫወት ይወዱ እንደነበር የሚነገርላቸው አቶ መለስ የመንግስታቸው ባለስልጣኖች ከባለሃብቶች ጋር ባደረጉት የእግር ካስ ጨዋታ ላይ ማሊያ ለብሰው ገምባሌ አጥልቀው ካስ መሊጋት ቀርቶ

አመት በላይ የመሩትን መሪ ለሞት የዳረገው ህመም ምን እንደሆነ እንዲሁም የሞቱበትን ትክክለኛ ጊዜ እስከዛሬ ድረስ አያውቅም። ይሄ እንደ ቢ.ቢ.ሲ. ያሉ አለማቀፍ መገናኛ ብዙሃንን ያስገረመ የኢህአዴግ ተፈጥሮ ነው። የአቶ መለስ ሞት ወዲው ያልተገለፀው አጋጣሚውን ተጠቅሞ ስልጣንን አደጋ ላይ ከሚጥል ነገር ለመጠንቀቅ ነው ቢባል እንኳን ከሁሉ በኋላ ህመማቸው ምን እንደነበረ፣ የት ሆስፒታል ምን አይነት ህክምና እንደወሰዱ ያለመነገሩ ነገር የፓርቲውን ሚስጥራዊ ተፈጥሮ ከማመላከት በዘለለ የፖለቲካ ፋይዳው እምብዛም ነው። የፓርቲው ልክ የለሽ ሚስጥራዊነት ግብ ዞሮ ዞሮ የስልጣንን እድሜ ከማስረዘም አያልፍም። ውስጥን ያወቀ ተገዳዳሪ በደካማ ጎን ገብቶ የስልጣንን እድሜ ሊያሳጥር ይችላል በሚል እሳቤ ይመስላል የኢህአዴግ ዝግነት የመጣው። በተቃራኒው የፓርቲ ዲሲፕሊን ያላቸው ከማይመስሉት አብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እለጣዝባ የውስጥ ፓርቲ ሁኔታቸውን ስለሚረዳ ከእግሩ በታች ለማድረግ አይቸገርም። በዚህ ረገድ የኢህአዴግ አመራሮች ከተቃዋሚዎቹ በተሻለ ለአላማ የመቆም ፅናት እንዳላቸው ይታየኛል። ምናልባት የኢህአዴግ አመራሮች የሚተባበሩት ከፖለቲካዊ አላማ ፅናት ይልቅ ኢኮኖሚያዊ ዋስትናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ነው የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን የኢህአዴግ አመራሮች ለአላማ መፅናት ኢኮኖሚያዊ ትርፍ በማይታሰበበት በጫካ ትግሉ ወቅትም የተመሰከረ ነው። ከስልጣን በኋላ ትብብራቸው ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ያለመ ነው ቢባል እንኳን እነሱ ለጥቅም ሲሉ ያደረጉትን ትብብር ተቃዋሚዎቹ ዲሞክራሲን መገንባትን ለመሰለ ትልቅ አላማ አብሮ መስራት ያቃታቸው ለምንድን ነው የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

የኢህአዴግ በማንኛውም ደረጃ ያሉን ተገዳዳሪ የመፍራት እና አበክሮ የመከታተል ተፈጥሮም ሌላው ለስልጣኑ ማገር የሆነው ባህሉ ነው። ነቃፊውን ሁሉ ከመከተታተሉ በተጨማሪ የበለጠ አደገኛ የሚሆነውን ነቅሶ ማውጣ እና አዳክሞ ማጥፋት ኢህአዴግ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ጠላቶቹን የሚያስወግድበት መንገድ ነው። በዚህ በኩል የኢህአዴግ አደን እስከ ግለሰቦች ሊደርስ ይችላል። በፓርቲ ባይታቀፉም፣ በምርጫ ባይወዳደሩም ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን ከዕይታ ማስወገድን ኢህአዴግ ተክኖበታል። ይህንንም የፓርቲው ያለመልፈስፈስ ብርታት ሲሉ ይገልፁት ነበር ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስተር። የማቆያ ዘዴው ምንም ሆነ ምን እንደ መጫኛ የረዘመ የስልጣን



ዘመን ከዲሞክራሲ ጋር ህብረት የለውም። ሃያ ምናምን አመት ፓርቲ ቀርቶ ሰው (መሪ)ሳይቀየር ስልጣን ላይ መኖር የዘመነ ፖለቲከኝነትም አይደለም።

# 4.6 የሃገራችን ልሂቃን ስልጣንን አረዳድ እና ፍላጎት

### ስልስቱ ፅንፎች

ኢህአዴግን ጨምሮ ኢትዮጵያችንን ለመምራት በትረስልጣን የጨበጡ መሪዎች የአለቅነትን አጀብ ግርግር የሚወዱትን ያህል በደረሰበት መድረስ የማይፈልጉ ወገኖችም አሉ። እነዚህ ሁለቱ ቡድኖች ስልጣንን በተመለከተ በሁለት ተቃራኒ ጥግ ላይ ያሉ አመለካከቶች ናቸው። በመሃል ላይ ያሉት ደግሞ ወደ ስልጣን ለመቅረብ ፓርቲ ይመሰርታሉ፣ ተከታይም ይኖራቸዋል፣ ስልጣን በያዘ አካል ላይ ሂስ ያቀርባሉ። ሲተቹ የነበረውን በተግባር ወደ ስልጣን መጥቶ ለማስተካከል ግን አይፈልጉም። እነዚህኞቹ የሚፈልጉት የሙሉ ጊዜ ተች መሆንን ነውና ስልጣን መያዝ አይሹም። በእርግጥ ለአንድ ሃገር በሁሉ ዘርፍ ሃያሲ ያስፈልጋታል። ሃያሲ ለመሆን ግን ፓርቲ መስርቶ መታገል አያስፈልግም። ፓርቲ መስረቶ የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርፆ መንቀሳቀስ ከተጀመረ ስልጣን ለመያዝ ማመንታት የሚጋጭ ነገር ነው።

## ፅንፍ አንድ፡ የስልጣን ፍቅር ልክፍት

### የማያውቁትን መናፈቅ

«የማያውቁት ሃገር አይናፍቅም» የሚለው ሃገርኛ ብሂላችን ሰዎች የሚጓጉት ለሚያውቁት፣ ለለመዱት ነገር ነው የሚል እሳቤን መሰረት ያደረገ አባባል ነው። በስልጣን ጉዳይ ግን ይህ እሳቤ የሚያስኬድ አይመስልም። ምክንያቱም ስልጣን ላይ ያለው ስልጣኑን ለማቆየት የሚጓጓውን ያህል በታሪክ ወደ ስልጣን መጥቶ የማያውቀውም የስልጣን እርካቡን ለመርገጥ ይለፋል። ስለ ስልጣንም ክቡሩን የሰው ልጅ ህይወት እስከማጥፋት ይኬዳል። ይሄ ሁሉ የስልጣንን ደጀሰላም መልካምነት እርግጠኛ ሳይሆኑ የሚደረግ አይደለም። እርግጠኝነቱ ግን እንደቶማስ ሄይቶ ብቻ ከማመን የመጣ አይደለም። ስልጣን እንዲህ ነው ሳያውቁትም ይናፈቃል፣ ሳቀምሱትም ይጣፍጣል። ለዛ ነው አዳሜ ስለ ስልጣን ነፍስ የሚዋደቀው፣ ባስ ሲልም ስልጣኑን የተመኘ የመሰለውን በጣውንት አይን የሚያየው።

ሳይንስ፣ በፍልስፍና እና በሌሎች ፖለቲካን በደበልጥ ለመረዳት በሚረዱ የትምህርት መስኮች ያሰለጠ እና እያሰለጠነ ያለ ቢሆንም ሃገራችን በቋሚነት ፖለቲካን የሚተነተኑ በቂ ባለሙያወች አሏት ማለት አይቻልም። በሰለጠነው አለም ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ሃገራቸውን የቀን ተቀን የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚተነትኑ ምሁራን የትየለሌ ናቸው። በተጨሪም ከፖለቲካው በአንድ መስክ የትኩረት አቅጣጫ (Area of specialization) ይዘው ስለሚሰሩ በእያንዳንዱ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ጥልቅ ማብራሪያ ማግኘት ቀላል ይሆናል። ይሄ ደግሞ የህዝብን ፖለቲካዊ ንቃት ለማሳደግ ይረዳል። እንደሰለጠነው አለም ለያንዳንዱ ፖለቲካዊ ሁነት በሙያው የሰለጠነ ተንታኝ ማግኘት ባይቻል እንኳን እንደ ሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እና የመስኩ ምሁራን ብዛት አሁን በሃገራችን እንደሚስተዋለው አይነት የተንታኝ ምሁራን ድርቅ መኖር አልነበረትም።

የምሁራኑ ወደ ስልጣን ከመምጣት ይቅርና በሃገራችን ፖለቲካዊ ዘይቤ ላይ ሙያዊ ትንታኔ ከመስጠት መሸሽ የሃገሪቱ ፖለቲካ በጥራዝ ነጠቆች እንዲዘወር አድርጎታል። በመስኩ ትምህርቱና ልምዱ ያላቸው እውቀት ልምዳቸውን ይዘው ሲሸሹ ካድሬነትንና እውቀትን እኩል ፈሰስ የደረገው የአሁኑ የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ካድሬነቱ ላይ የበረታ ሁሉ በመሰለው መንገድ እየነዳ ሃገሪቱን ከቀን ወደ ቀን በሚባባስ ግራ መጋባት ውስጥ ከቷታል። ስልጣን ከጨበጠው አካል የአቅም ውሱንነቶች የተነሳ ሃገራችን የጠራ የፖለቲካ መስመርም ሆነ የተረጋጋ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የላትም። መንግስት እከተለዋለሁ የሚለውን ርዕዮተ አለም -አብዮታዊ ዲሞክራሲን ህዝቡ ቀርቶ ጎላ ያለ ስልጠን የያዙ ካድሬዎቹ እንኳን በቅጡ የሚያውቁት አይመስልም። የኢኮኖሚ ፖሊሲውም ነፃ ገበያ ሲሉት ዕዝ ኢኮኖሚ እየመሰለ ሚናውን ሳይለይ ዘመናትተቆጠሩ። በስተመጨረሻው ደግሞ የገዥው ፓርቲ ቀዳሚ ባለስልጣን አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ትርጉሙ ግልፅ ባይሆንም መንግስታቸው የልማታዊ መንግስት ፖለቲካል ኢኮኖሚን ለመገንባት እየሰራ እንደሆነ ተናግረዋል። በሃገሪቱ የሚወጡ ፖሊሲዎች በስራ ላይ ውለው ያመጡት ጥቅም እና ጉዳት የመመርመር ስራ (Impact Assesment) የሚደረግበት ፋታ ሳያገኙ በሌላ ይተካሉ። ‹አንችው ታመጭው አንችው ታሮጭው› አይነት ነገር በዝቷል። ይሄ ሁሉ የአካሄድ ዝብርቅርቅ ዋነኛ ምክንያቱ ምሁራን ከስልጠን እና ተያያዥ ፖለቲካዊ ጉዳዮች መሸሽ ስለሆነ



ምሁራኑ የተጠናወታቸው ከስልጣን የመሸሽ አይነ-ጥላ እስካልተገፈፈ ድረስ የሚቀጥል እውነታ ነው።

## ፅንፍ ሶስት፡ የተጠጌ አይነኬዎች

ስልጣን አጥብቆ በመውደድ እና አብዝቶ በመፍራት ሁለት ፅንፎች መሃከል ወደ ስልጣን የሚጠጉ፣ ፓርቲ የሚመሰርቱ፣ ስለለውጥ አስፈላጊነት የሚሰብኩ ነገር ግን ስልጣንን መያዝ አንፈልግም የሚሉ ሶስተኛ ፅንፈኞችም አሉ። እነዚህ ወገኖች በየዘመኑ ስልጣን የያዘነው አካል ይተቻሉ። በበዕሁፋውም ሆነ በአደባባይ ንግግራቸዉ መልካም የሆኑ አማራጭ ሃሳቦች ይሰነዝራሉ። እያይዘውም ስልጣን ላይ መውጣት እንደማይፈልጉ፣ የስልጣን ጥመኞች እንዳልሆኑም ይናገራሉ።

በግሌ ስልጣንን መሻት በራሱ ችግር አይደለም። እንደውም ስልጣንን ከሚሸሹት ስልጣን የሚሹት በተሻለ ሃላፊነት ለመሸከም የተዘጋጁ ናቸው። ዋናው ጥያቄ ስልጣኑን ለምን ፈለጉት ሚለው ነው። ስልጣን መሻቱ ስልጣን ላይ ተወዝፎ ለመሰንበት፣ «የእግዜር ታናሽ» የሁሉነገር አድራጊ ፈጣሪ አምባገነን ለመሆን፣ የህዝብን ችግር በመፍታት ፋንታ ራሱን እና ደቀመዛሙርቱን ብቻ በምቾት ማማ ላይ ለማውጣት ከሆነ ስልጣን መሻቱ ለበጎ አይደለም እና በስልጣን ጥመኝነት ሊያስወቅስ ይችላል።

ነገር ግን የስልጣን ጥም የለብኝም በሚል ሰበብ ለሃገር ብዙ ሊያበረክቱ የሚችሉ ምሁራን እውቀት እና ልምድ ሲባክን ያሳስባል። እነዚህ ስልጣን አንፈልግም ባይ ምሁራን ተገቢ ቦታቸውን ስላልያዙ የሃገሪቱ ሁለንተናዊ ጉዞ አላዋቂነት የበዛበት፣ ከሳይንሳዊ መንገድ ይልቅ ፕሮፖጋንዳ የገነነበት ሆኗል። ትቂት ሰርቶ ብዙ መኩራራቱም ከዚሁ ከእውቀት ጋር ከመራራቅ የመጣችግር ነው። ከዚህ የተነሳም ሃገራችን የተፈጥሮ ሃብታምነቷን እና ታሪካዊ ታላቅነቷን በማይመጥን ዝቅታ ላይ ትገኛለች።

ዝቅታው ደግሞ ከማንም በላይ ከስልጣን የሚሸሹትን ምሁራን ያስቆጫል። ወደተስፋ መቁረጥ የቀረበውን ቁጭታቸውን ለመረዳት ከሚፅፏቸዉ መፅሃፍት ውስጥ አንድ ሁለቱን ገፅ ማንበብ ይበቃል። በሀገራችን ለተከሰተው ሁለንተናዊ ጭንገፋ የእነሱ ከስልጣን ሽሽት አንዱ ምክንያት መሆኑን ግን የተረዱ አይመስልም። በምትኩ ከስልጣን ሽሽታቸውን ስንቱ ከተረታባት

